## የይግባኝ መብቶች (APPEAL RIGHTS)

የWashington አስተዳደራዊ ኮድ (Washington Administrative Code, WAC) 388-02-0525 እና የWashington የተሻሻለው ኮድ (Revised Code of Washington, RCW) 34.05.464 ስር፣ ይህ ትዕዛዝ ደብዳቤው ከተላከበት ቀን ከ21 የቀን መቁጠሪያ ቀናት በኋላ የመጨረሻ ይሆናል።

1. ይህ የትዕዛዝ ደብዳቤ ከተላከበት 21 የቀን መቁጠሪያ ቀናት በኋላ እርስዎ ወይም ማንኛውም ወገን ይግባኝ (የግምገማ ጥያቄ) ለይግባኝ ሰሚው ቦርድ ካላስገቡ በስተቀር (ከላይ ባለው የአገልግሎት መግለጫ ላይ ደብዳቤ የመላኪያ ቀንን ይመልከቱ)፤ ወይም
2. እርስዎ ወይም ማንኛውም ወገን የ21 ቀን የጊዜ ገደብ እንዲራዘም ጥያቄ አቅርበው የግምገማው ዳኛ በWAC 388-02-0580(2) መሰረት ለማራዘሚያ የሚሆን በቂ ምክንያት እንዳላችሁ ካልወሰኑ በስተቀር፤ ወይም
3. ከ21-ቀን የጊዜ ገደብ በኋላ 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርስዎ ወይም ማንኛውም ወገን የዘገየ የግምገማ ጥያቄ አቅርበው የግምገማ ዳኛው በWAC 388-02-0580(3) መሰረት ግምገማ ዘግይታችሁ ለመጠየቃችሁ በቂ ምክንያት እንዳላችሁ ካልወሰኑ በስተቀር።

የግምገማ ጥያቄ ለማቅረብ ደብዳቤ መላኪያ አድራሻው የሚከተለው ነው፡-

ይግባኞችን ሰሚ ቦርድ
P.O. Box 45803
Olympia, WA 98504-5803

የግምገማ ጥያቄ ለማቅረብ ከመረጡ፣ ከዚህ ትዕዛዝ ጋር ያለውን ቅጽ እና መመሪያዎች ሊጠቀሙ ይችላሉ።

ናሙና

**ይህ ከተቀበሉት ሰነዶች ጋር ለማነፃፀር የሚያግዝዎትን አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ ምሳሌ ነው።**

## **የመጀመሪያ ውሳኔ እንዲገመገም አቤቱታ (ይግባኝ) (PETITION FOR REVIEW OF INITIAL DECISION (APPEAL)**

ዝርዝር መልሶችን ያትሙ ወይም ይተይቡ። አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ገፆችን ያክሉ። የራስዎን ቅጽ መጠቀም ይችላሉ።

| ______________________________ | የጉዳይ ቁጥር | ______________ |
|---|---|---|
| ስም(ሞች) (እባክዎ ያትሙ) | የዶሴ ቁጥር | የኤጀንሲ ቁጥር |

| ______________________________ | | | |
|---|---|---|---|
| የደብዳቤ መላኪያ አድራሻ | ከተማ | ግዛት | ዚፕ ኮድ |

______________________________

የስልክ አካባቢ ኮድ እና ቁጥር

እባክዎ የመጀመሪያ ትዕዛዝ እንዲቀየር ለምን እንደፈለጉ ያብራሩ። ግልጽ ለመሆን ይሞክሩ። ለምሳሌ፣ የሚከተለውን ይንገሩን፦

1. ውሳኔው የተሳሳተ ነው ብለው ያሰቡት ለምንድን ነው (ከእሱ ጋር የማይስማሙት ለምንድን ነው)።
3. ውሳኔው እንዴት መቀየር እንዳለበት።
2. የትኞቹ የእውነታ ግኝቶች የተሳሳቱ ናቸው።

የመጀመሪያውን ውሳኔ እንዲገመገም እጠይቃለሁ ምክንያቱም...

___ ገፆችን አያይዤያለሁ።

| ______________________________ | | |
|---|---|---|
| ስምዎን ያትሙ | ፊርማ | ቀን |

**ቀነ ገደብ፦ የመጀመሪያ ውሳኔ በደብዳቤ ከተላከበት ቀን ጀምሮ በ21 ቀናት ወይም ከዚያ በፊት የደረሰ**

በደብዳቤ የተላከው ለ፦ ይግባኞችን ሰሚ ቦርድ
P.O. Box 45803
Olympia, WA 98504-5803

ናሙና

**ይህ ከተቀበሉት ሰነዶች ጋር ለማነፃፀር የሚያግዝዎትን አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ ምሳሌ ነው።**

ካልተስማሙ
ይግባኝ ማለት ይችላሉ

1. **<u>የይግባኝ ቀነ ገደብ</u>**፡- ይግባኝ ሰሚ ቦርዱ በተያዘው የችሎት ውሳኔ ላይ ከተመለከተው ደብዳቤ መላኪያ ቀን ጀምሮ ባሉት ሃያ አንድ (21) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ይግባኝዎ <u>ሊደርሰው</u> ይገባል። በ21 ኛው ቀን ላይ ወይም ከዚያ በፊት ሊደርስ ይገባል አለበለዚያ ይዘገያል እና ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል። ለማድረስ ጊዜ ለመስጠት እባክዎ ከቀነ ገደቡ በፊት በደብዳቤ ይላኩ። ቀነ ገደቡ ካመለጠዎት፣ ውሳኔውን ይግባኝ የማለት ሁሉንም መብቶች ሊያጡ ይችላሉ።

2. **<u>ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልግዎ ከሆነ</u>**፡- የግምገማ ዳኛ ቀነ-ገደቡን ማዘግየት (ማስተላለፍ፣ ማራዘም) ይችላሉ፣ ነገር ግን በሃያ አንድ (21) ቀን የጊዜ ገደብ ውስጥ መጠየቅ አለብዎት።

3. **<u>ማን ይግባኝ ማለት እንደሚችል</u>**፡- በአጠቃላይ ማንኛውም ውሳኔው በቀጥታ የሚነካው ሰው።

4. **<u>እንዴት ይግባኝ ማለት እንደሚቻል</u>**፡- የተዘጋውን ቅጽ ይጠቀሙ ወይም የራስዎን ያዘጋጁ። ይግባኙን ወደ ይግባኞችን ሰሚ ቦርድ መላክ ወይም ማድረስ አለብዎት (ከዚህ በታች ያለውን አድራሻ ይመልከቱ)። ቅጂ ማስቀመጥዎን እርግጠኛ ይሁኑ።

5. **<u>ለሌሎች ወገኖች የሚላኩ ቅጂዎች</u>**፡- በዚህ ጉዳይ ውስጥ ላለ ማንኛውም አካል የይግባኙን (እና ዓባሪዎች) ቅጂ መላክ ወይም ማድረስ አለብዎት።

6. **<u>ቀጥሎ ምን ይሆናል</u>**፡- ይግባኞችን ሰሚ ቦርድ ይግባኝ ወይም የተጨማሪ ጊዜ ጥያቄ ሲደርሰው ለሁሉም ወገኖች ያሳውቃል። የግምገማ ዳኛ (Review Judge, RJ) ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ ሁሉንም ወረቀቶች ያነባሉ እና የችሎቱን የድምጽ ቅጂ ያዳምጣሉ። እንዲሁም RJ ህጉን እና ወገኖቹ የሚያቀርቡትን ክርክር ይመለከታል። RJ አዲስ ማስረጃ (ማለትም በችሎቱ ላይ ያልታየ ነገር) መታየት አለመታየቱን ሊወስኑ ይችላሉ። <u>RJ አዲስ ችሎት አያካሂድም</u>። ከዚያም RJ ውሳኔውን ጽፈው ለሁሉም ወገኖች በደብዳቤ ይልካሉ። RJ ይግባኝ እየተባለ ባለው ውሳኔ ሊስማሙ ወይም ሊለውጡት ይችላሉ። RJ አዲስ ችሎት እና/ወይም አዲስ ውሳኔ ሊያዙ ይችላሉ። በይግባኙ ላይ በRJ ውሳኔ ካልተስማሙ፣ ለበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ወይም RJ እንደገና እንዲያጤኑት ወይም ሁለቱንም መጠየቅ ይችላሉ። የግምገማ ውሳኔ ሲደርስዎ ስለ የይግባኝ መብቶች ቀጣይ ደረጃ ተጨማሪ መረጃ ያገኛሉ።

7. **<u>እገዛ የሚያስፈልግዎ ከሆነ</u>**፡- በችሎቱ ላይ የሚወክልዎት ሰው (እንደ ጠበቃ ወይም ጓደኛ ያለ) ካለዎት፣ እሱን ወይም እሷን ያነጋግሩ። ጠበቃ ወይም የህግ ምክር ያስፈልገኛል ብለው ካሰቡ፣ የሰሜን ምዕራብ ፍትህ ፕሮጀክት (Northwest Justice Project) የተቀናጀ የህግ ትምህርት፣ ምክር እና ሪፈራል (Coordinated Legal Eduction, Advice and Referal, CLEAR) የስልክ መስመርን (888) 201-1014 ላይ ያግኙ። በነፃ ጠበቃ የማግኘት ዋስትና የለዎትም።

8. **<u>ትርጉሞች እና የዕይታ ችግሮች</u>**፡- እንግሊዘኛ የማየነቡ እና የማይጽፉ ከሆነ፣ በራስዎ ቋንቋ ወረቀቶችን ማስገባት እና መቀበል ይችላሉ። አልታይ ካለዎት እንደ ብሬይል ወይም ትልቅ ህትመት ባሉ ተለዋጭ ቅርጸቶች ወረቀቶችን የማስገባት እና የመቀበል መብት አለዎት። የእርስዎን ፍላጎት ለይግባኞችን ሰሚ ቦርድ ያሳውቁ።

**ይግባኝዎን (የግምገማ ጥያቄ) ወደ የይግባኝ ቢሮ ይላኩ ወይም ያቅርቡ፡-**

| <u>የደብዳቤ መላኪያ አድራሻ</u> | <u>የግል አገልግሎት አካባቢ</u> |
|---|---|
| ይግባኞችን ሰሚ ቦርድ<br>P.O. BOX 45803<br>OLYMPIA WA 98504-5803 | የDSHS ይግባኞችን ሰሚ ቦርድ<br>1115 Washington Street SE<br>Olympia, Washington 98501 |
| <u>ፋክስ</u><br><br>1-360-664-6187 | <u>ስልክ (ለበለጠ መረጃ)</u><br>1-360-664-6100<br>1-877-351-0002 (ከክፍያ ነፃ) |

**ይህ ከተቀበሉት ሰነዶች ጋር ለማነፃፀር የሚያግዝዎትን አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ ምሳሌ ነው።**